መመሪያ ቁጥር 08/2010

**በልውጥ ሕያዋን እንቅስቃሴዎች ላይ ለመሰማራት የሚቀርቡ ማመልከቻዎች ይዘትን ለመወሰን የወጣ መመሪያ**

በልውጥ ሕያዋን እንቅስቃሴ ለመሰማራት የሚቀርቡ የፈቃድ ጥያቄ ማመልከቻዎችን ዋና ዋና ይዘት መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአካባቢ፣ የደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር ስለደሕንነት ሕይወት በወጣው አዋጅ ቁጥር 655/2001 (በአዋጅ ቁጥር 896/2007 እንደተሻሻለው) አንቀጽ 25 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "በልውጥ ሕያዋን የተጤነ ልቀት እንቅስቃሴዎች ለመሰማራት የሚቀርቡ ማመልከቻዎች ይዘት መወሰኛ መመሪያ ቁጥር 08/2010" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **የተፈፃሚነት ወሰን**

   ይህ መመሪያ ያለምንም ክልከላ ወደ አካባቢ በሚለቀቁ ማናቸውም ልውጥ ሕያዋን እንቅስቃሴ ላይ ለመሰማራት በሚቀርቡ ማመልከቻዎች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

3. **አጠቃላይ መረጃዎች**

   በልውጥ ሕያዋን የተጤነ ልቀት እንቅስቃሴዎች ላይ ለመሰማራት የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን አጠቃላይ መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፤

   1/ ስም፣ አድራሻ እና አመልካቹ የሚገኝበት ዝርዝር መረጃ፤

   2/ ፕሮጀክቱን ለማቀድና ለመተግበር፣ እንዲሁም ለቁጥጥር፣ ለክትትል እና ለደኅንነት ኃላፊነት ያለባቸው ባለሙያዎች ስም፣ የሥልጠና መስኮች በተለይም የኃላፊው ሳይንቲስት ስም።

የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር
Ministry of Environment, Forest and Climate Change

## ክፍል ሁለት

## የሰጪ ሕያው፣ የተቀባይ እና የልውጥ ሕያው መረጃ

### 4. የሰጪ ሕያው፣ የተቀባይ እና ልውጥ ህያዉ መረጃዎች

የሰጪ ሕያው፣ የተቀባይ እና ልውጥ ህያዉን በተመለከተ የሚከተሉት መረጃዎች በአመልካቹ መቅረብ አለባቸው፤

1/ ሰጪ የሆነው ሕያው ሳይንሳዊ ስም፣ የተሰጠው ከሆነም የተለምዶ ስም፤

2/ ተቀባይ የሆነው ልውጥ ሕያው ሳይንሳዊ ስም፣ የተሰጠው ከሆነም የተለምዶ ስም፤

3/ በክስተት ጥንቅሩ ውስጥ የተካተቱ ባይተዋር ዘረመሎች ምንጮች ከሆኑት ማናቸውም ሕያዋን ጋራ የሚዛመዱ ዝርያዎች ሳይንሳዊ ስሞችና የተሰጣቸው ከሆነም የተለምዶ ስሞች፤

4/ ተቀባይ እና ሰጪ (ወላጆች) ሕያዋን ያላቸው የመመሳሰል ደረጃ፤

5/ ሰጪ እና የተቀባይ (ወላጆች) ሕያዋን መልካአ ምድራዊ ሥርጭት፣ የተፈጥሮ መገኛ ቦታ ወይም የሚከሰትበት አካባቢ::

### 5. የባህርይ ክስተትን የሚለውጡ ኑክሊክ አሲዶች ባህርያት

የባህርይ ክስተትን የሚለውጡ ኑክላይክ አሲዶች ባህርያትን በተመለከተ የሚከተሉት መረጃዎች በአመልካቹ መቅረብ አለባቸው፤

1/ የእያንዳንዱ ዘረመል ክስተት ጥንክር ዝርዝር መግለጫ፤

2/ ኑክሊክ አሲዱ ምንም ለውጥ ሳይደረግበት ወደ ህያው መግባቱ፣ ወይም ልውጥ ከሆነም ኑክለይክ አሲዱን ለመለወጥ ሥራ ላይ የዋለው ዘዴ፤

3/ የኑክሊክ አሲዱ ቅደም ተከተል፣ በተለይም በዋናው ዘረመል፣ በፕሮሞተር፣ በተርሚኔተር ዘረ-መሎች፣ እና መምረጫ ዘረመላዊ ምልክት በመሳሰሉት፤

4/ የኒክሊክ አሲዱ የሚወክለው ባሕሪይ መገለጫ ዝርዝር መረጃ

5/ የባሕሪይ ምንነቱን ለመሥራት ሥራ ላይ የዋለው ዘዴ፤

6/ ዘረመላዊ ምልክቶች፤

7/ ዘረመሉ መኖር ወይም አለመኖሩን ማወቅያ እና መለያ ዘዴዎች መግለጫ፤